# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ህዳር 2 ቀን 2004 ዓ.ም**

**ህዝቡ በርሀብ እያለቀ በእርዳታ ጅቡቲ ወደብ የገባው ስንዴ ሳይነሳ እየበሰበሰ መሆኑ ተጋለጠ፤**

**የኢትዮጵያዊውን ህይወት የታደገው እውቁ ድምፃዊ ቲዲ አፍሮ በወያኔ ውግዘት ደረሰበት፤**

**ህዝቡ በወያኔ ላይ እምነት በማጣቱ ገንዘቡን ከባንክ እያወጣ መሆኑ ተጠቆመ፤**

ህዝብ በርሀብ እና በችጋር እየተጠቃ ባለበት በዚህ ግዜ የእርዳታ እህል ከለጋሽ ሀገሮች ጅቡቲ ወደብ ቢደርስም ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባው ጠፍቶ እየተበላሸ መሆኑ ተጠቆመ።

ወያኔ የስልጣን እድሜ ማራዘሚያ ብሎ በፈጠራቸው ሰንካላ ምክንያቶች የተነሳ ከጅቡቲ ወደቦች የስንዴው እህል በወቅቱ ተነስቶ በአግባቡ ለተረጂው ህዝብ እንዳይደርስ ደንቃራ እየፈጠረ መሆኑን የጠቆሙት የከባድ መኪና አሽከራካሪዎች ሰሞኑን ማንኛውም ከባድ መኪና ሲሚንቶ እና ብረት ብቻ ጭኖ እንዲመጣ ተብሎ መታዘዙን አጋልጠዋል።

ከግንባታ በፊት የዜጎችን ህይወት መታደግ ቅድሚያ የሚሰጠው መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑ እየታወቀ የእድሜ ማራዘሚያ አድርገው የፈጠሩት የአባይ ግድብ ግንባታ ተብሎ ከውጭ የመጣ ብረት እና ሲሚንቶ በግዴታ የጭነት መኪኖች እንዲጭኑ እየተደረገ መሆኑን ሹፌሮቹ አጋልጠዋል።

በልመና እና በእርዳታ ጅቡቲ ወደብ የገባው ስንዴ የሚያነሳው ጠፍቶ በመርከብ እና በወደቡ ላይ ተራግፎ በውሀ እየተበላሸ ከመሆኑም በተጨማሪ በጅቡቲ ዘራፊዎች እየተበዘበዘ መሆኑን የጠቆሙት ሹፌሮቹ በተለይ በአሁኑ ሰዓት መላው የሀገሪቱ ህዝቦች በከፍተኛ የኑሮ ውድነት እየተሰቃዩ ባለበት ግዜ እንዲሁም በቦረና ህዝብ እያለቀ መሆኑ እየታወቀ ለአባይ ግንባታ ቅድሚያ ይሰጠው ተብሎ መኪኖቹን በግዳጅ ሲሚንቶና ብረት እንዲጭኑ ማስገደዳቸው በእጅጉ የሚያሳዝን እና ለዜጎች ህይወት ክብር እንደሌላቸው ያሳየ ነው ሲሉ ሹፌሮቹ በቁጭት እየተናገሩ ይገኛሉ።

በአሁኑ ሰዓት በቦረና እና በጎዴ ህዝብ እና ከብት እያለቀ መሆኑን የረድኤት ድርጅት ሰራተኞች ያረጋገጡ ሲሆን ቅድሚያ ለዜጎች ህይወት ማዳን ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መረባረብ ሲገባ የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት ወደ ጎን ብለው የዓለም አቀፍ መንግስታትን ለመሸንገል እና ለስልጣን እድሜ ማራዘሚያቸው ሲሉ ብቻ ከጅቡቲ ወደብ ብረት እና ሲሚንቶ እንዲጉዋጉዋዝ ማድረጋቸው አሳዛኝ እና አሳፋሪ መሆኑንም ሹፌሮቹ በብስጭት ይገልፃሉ።

ህዝቡ በርሀብ እያለቀ ቅድሚያ ስንዴው እንዲገባ ከማድረግ ይልቅ ሲሚንቶና ብረት ይቅደም መባሉ ወያኔ ከደረሰበት ውስጣዊና ውጫዊ ፖለቲካ ኪሳራ መጠገኛ ሊሆነኝ ይችላል ከሚል አናሳ አስተሳሰብ በመነጨ ፍላጎት ጭምር ዜጎች አይናቸው እያየ እየሞቱ እንደሚገኙና አሁንም አስቸኩዋይ እርዳታ ካልደረሰላቸው በሺህዎች የሚቆጠሩት ሊሞቱ እንደሚችል የረድኤት ድርጅት ሰራተኞች ስጋታቸውን እየገለፁ ቢገኙም ለዜጎች ክብር የሌለው ይሄው የወያኔ ቡድን አሁንም በአስቸኩዋይ ብረቱና ሲሚንቶው ወደ ግድቡ ይጉዋጉዋዝ በሚል መኪኖቹን እያስገደደ መሆኑን ከሹፌሮቹ ለመረዳት ተችሎዋል።

በሀገር ውስጥ ያሉ ከባድ መኪኖች ባዶዋቸውን በግዴታ ወደ ጅቡቲ እንዲወጡ እያስገደዱ እንደሚልኩዋቸውና ጅቡቲ ሲገቡ ደግሞ በቀጥታ ወደብ ድረስ አስገድደው ብረት እና ሲሚንቶ የሚያስጭኑዋቸው ሲሆን ለሹፌርና ረዳቶቻቸው አበልና ሌሎች ወጪዎችን ሳይሰጡ በባዶ እጃቸው ብቻ እንዲወጡ እያደረጉዋቸው በመሆኑ በከፍተኛ ምሬት ላይ እንደሚገኙ ከሹፌሮቹ ገለጻ ለማወቅ ተችሎዋል።

ከጅቡቲ ተነስቶ የአባይን በረሀ ለመውጣት ሰዓታት ሳይሆን ቀናትን እንደሚፈጅ እያወቁ ያለ አንዳች ሀዘኔታ በግዳጅ ያለ አበል ውሰዱ መባሉ እስከ ዛሬ ድረስ ታይቶና ተሰምቶ ያልታወቀ ከመሆኑም በላይ ናዚያዊ አስተዳደር በላያችን ላይ መጫኑን እያረጋገጥን ነው ያሉት ሹፌሮቹ ለችግር ግዜ ይሆናል......ለልጆቻችን መታከሚያ ይሆናል...... ለክፉ ቀን ብለን ቤተሰቦቻችን ጋር ያስቀመጥነውን ሳንቲም እያወጣን ለመጠቀም ተገድደናል ሲሉም እንባ እየተናነቃቸው ሲናገሩ ተደምጠዋል።

በአሁኑ ሰዓት መላው የሀገሪቱ ህዝቦች በከፍተኛ የኑሮ ውድነት ከመቸገራቸውም በተጨማሪ የእለት ጉርስ የሚሆን ዳቦ እንኩዋን ጠፍቶ ከአዲስ አበባ ጀምሮ እስከ ክልል ከተሞች ድረስ በረዣዥም ሰልፎች እየታዩ ከመሆኑም በተጨማሪ ሳይደርሳቸው ባዶ እጃቸውን የሚመለሱ ዜጎች ቁጥር ቀላል እንዳልሆነም እየተገለፀ ነው።

በወያኔ ባለስልጣናት ድርጊት የተበሳጩት የከባድ መኪና ሹፌሮቹ መኪኖቻቸውን መንገድ ላይ እያበላሹ እያቆሙ ተቃውሞዋቸውን እየገለጹ ሲሆን በትንሹ በመቶዎች የሚቆጠሩት በእንደዚህ ባለ ሁኔታ ቁጣቸውን እየገለጹ መሆናቸውንም ሹፌሮቹ ተናግረዋል።

የመኪና ባለቤቶች በበኩላቸው በግዳጅ ወደ አባይ መኪኖቻቸው እንዲጭኑ ሲደረግ እንደማያውቁና የክፍያው መጠን ስንት እንደሆነ ያልተነጋገሩ በመሆኑ የዜጎችን መብት በጣሰ መልኩ እንዲህ ያለ ግዳጅ ውስጥ መክተታቸው የሚያሳዝን መሆኑን የጠቀሱት ባለንብረቶቹ ዓመታዊ ግብር

እና ሌሎች ተዛማጅ ክፍያዎች ላይ ግዜ ሳይሰጡ እንደሚቀበሉ እያወቁ ዛሬ ከእኛ እውቅና ውጭ በግዴታ ማዘዛቸው አስገራሚ ነው ሲሉም ይናገራሉ።

በሌላ ዜና ሰው በመግደል ተጠርጥሮ ለአንድ አመት ታስሮ የቆየውና በመጨረሻም የሞት ፍርድ የተወሰነበትን ኢትዮጵያዊ የታደገው እውቁ አርቲስት ቴዲ አፍሮ ከወያኔ ባለስልጣናት ዛቻ እና ማስፈራሪያ እየተሰነዘረበት መሆኑ ታወቀ።

በሱማሌ ላንድ ውስጥ በንግድ ስራ ተሰማርቶ የነበረው የትግራይ ተወላጁ ኢትዮጵያዊ በሱማሌ ዜጎች የተቃጣበትን ጥቃት ለመመከት በወሰደው እርምጃ አንድ ሰው በመሞቱ ለአንድ ዓመት ያህል በእስር ቤት ከመማቀቁም በተጨማሪ በቅርቡ የሞት ፍርድ ወይም 40 ሺህ ዶላር ካሣ እንዲከፍል በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት እውቁ ድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን(ቴዲ አፍሮ) በግሉ ገንዘቡን ከፍሎ ህይወቱን ሊታደግ ቢችልም የወያኔ ባለስልጣናት ግን ህዝቡን ሊያነሳሳብን ነው በሚል የፈጸመውን ሰብአዊ ተግባር ወደ ወንጀል እያዞሩበት መሆኑ ታውቆዋል።

የቀድሞዋ የሱማሌ አካል የነበረችውና  የራስዋን አስተዳደር የመሰረተችው ፑንትላንድ አስመሮም ኃይለ ሥላሴ በተባለው ኢትዮጵያዊ ላይ የሞት ፍርድ ወይም 700 ሺህ ብር ካሣ እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥታ እለተ ሞቱን እየተጠባበቀ ባለበት ሰዓት እና የግዜ ገደቡ ሊያበቃ 3 ቀናት ሲቀረው እውቁ ድምጻዊ ቴዲ አፍሮ በግሉ በወሰደው አፋጣኝ የነፍስ ማዳን እርምጃ ብሩን የከፈለ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ከእስር እንዳልተፈታ ታውቆዋል።

በሰው መግደል ወንጀል ተከስሶ በሞት እንዲቀጣ የተወሰነበት ኢትዮጵያዊ ለአንድ ዓመት በእስር ቤት ውስጥ ሲማቅቅ መኖሩን የወያኔ ባለስልጣናት እያወቁ ጉዳዩን አፍነው እና በምስጢር ይዘው የነበረ ሲሆን ቅጣቱ ተፈጻሚ ሊሆን ቀናቶች ብቻ ሲቀረው ይፋ በመውጣቱና እውቁ ድምጻዊ ቴዲ አፍሮ በመታደጉ የተበሳጩት እነ በረከት ስምኦን በራዲዮ ፋና በኩል አንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቃል አቀባይን አቅርበው ህይወቱን ለመታደግ ሲጥሩ እንደነበር ከመግለፃቸውም በተጨማሪ ጥረታቸውን ቴዲ ድንገት መሀል ገብቶ መና እንዳደረገው ከፍተኛ ቅስቀሳ እየተሰራበት መሆኑም ታውቆዋል።

በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ እያለ ባለቤቱን ለመድፈር የመጡ የሱማሌ ጎረምሶችን ለመከላከል በወሰደው እርምጃ አንድ ሱማሊያዊ ዜጋ በመሞቱ ተከስሶ ሞት የተፈረደበትን አስመሮም ኃይለስላሴን የወያኔ ቡድን እንዲታደገው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ድረስ ዘልቀው በተደጋጋሚ ቢመጸኑም ሰሚ ሳያገኙ የቀሩት ቤተሰቦቹ ዛሬ እውቁ ድምፃዊ ባደረገው ድጋፍ ልጃቸው በመትረፉ ደስታቸውን እየገለፁ የሚገኙ ት ቤተሰቦቹ ይሄንንም ጉዳይ ከእንግዲህ ወዲያ የተደረገላቸውን ድጋፍ በሚዲያ በተለይ በነፃ ፕሬስ ጋዜጦች ላይ ምንም አይነት አስተያየት እንዳይናገሩ ማስጠንቀቂያ በደህንነቶች እንደተሰጣቸው ለቤተሰቡ ቅርበት  ካላቸው ወገኖች የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል።

የወያኔ ቡድን ልጃቸውን እንዲያተርፍላቸው ተደጋጋሚ ልመና እና ተማፅኖ ሲያቀርቡ የነበሩት ቤተሰቦቹ ቴዲ ባይታደገን ኖሮ ዛሬ ምናልባትም አስከሬኑን እንታቀፍ ነበር ያሉት እነዚሁ ቤተሰቦች አሁንም ካሳው ከተከፈለ በሁዋላ እንኩዋን ሌላ ቅድመ ሁኔታ አቅርበው አንፈታም እያሉ

በሚዝቱበት በዚህ ግዜ መንግስት ጣልቃ ገብቶ ለማስፈታት አለመሞከሩ ለዜጎቹ ያለውን ንቀት እና ጥላቻ እንደሚያሳይ በግልጽ እየተናገሩ ይገኛሉ::

አሁን ደግሞ አሉ እነዚሁ የአስመሮም ቤተሰቦች አሁን ደግሞ የጎሳ መሪዎቹ ትዕዛዝ ነው ተብሎ እህቱን ካልዳራችሁልን አንፈታም ብለው ሌላ አዲስ ትዕዛዝ መሰጠቱን እያወቁ በዜጎች ደም እጃቸው የጨቀየው ባለስልጣናቱ......በሙስና ኪሳቸው ያበጠው የወያኔ ቡድን መሪዎች ግን አሁንም መፍትሔ ለመስጠት ፍጹም ዝግጁ አይደሉም እያሉም እያነቡ መሆናቸው ታውቆዋል::

የጎረቤት ሀገር ሱማሌ ዜጎች እንዳሻቸው በኢትዮጵያ ውስጥ ዜጎቻችንን በአሰቃቂ ሁኔታ እየገደሉና እየዘረፉ ባለበት በዚህ ግዜ ሳይከሰሱና ሳይታሰሩ ይልቁንም ሰፊ ከለላና ሽፋን እየተሰጣቸው አንድ ኢትዮጵያዊን ለማስፈታት ዓመታትን ማስቆጠራቸው በእጅጉ የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን የሚያሳፍር ነው ሲሉም በንዴት ይገልጻሉ::

እውቁ ድምፃዊ በጎ አድራጎት ስራ ለመስራቱ ሊመሰገን እና ሊወደስ ሲገባው ይባስ ብለው ህዝቡን ሊያሳምጽብን ሆን ብሎ የሰራው ነው ብለው በራዲዮ ፋና እና በሌሎችም ሚዲያዎች የስም ማጥፋት ዘመቻ መክፈታቸው የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት ጭንቅላታቸው ባዶ መሆኑን ያሳየ ነው ያሉት አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር እነዚህ ሰዎች ምን ሊጥማቸው እንደሚችልና ምን እንደሚያስደስታቸው ግራ የሚያጋቡ ናቸው ሲሉም ተችተዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ወያኔ ግራ ገብቶት ህዝቡን ግራ እያጋባ ባለበት በዚህ ግዜ አዲስ ባወጣው የመሬት አስተዳደር ጋር በተያያዘ በተለይ ከአዲስ አበባና ናዝሬት ከተሞች ህዝቡ ተቀማጭ ገንዘብ እያወጣ መሆኑ ታወቀ::

በተለይ ከናዝሬት ከተማ የንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ከ75 በመቶ በላይ የሚሆኑት የባንኩ ደንበኞች ገንዘቡን እያወጡ በቤት እያስቀመጡ ከመሆናቸውም በላይ የወያኔ ቡድን ከበረሀ የመጣ ሽፍታ ኃላፊነት ስለማይሰማው በአንድ ጀንበር ተቀማጭ ገንዘብ ቢወርስ የማን ያለህ እንላለን እያለ ህዝቡ እየተነጋገረ እንዳወጣውም ከተለያዩ የንግድ ባንኩ ቅርንጫፎች የደረሱን ጥቆማዎች ገልፀዋል::

የመርካቶ ነጋዴዎች እና የሀገሪቱ ሀብታሞች በወያኔ ላይ እምነት ስለሌላቸው ገሚሱ ወደ ዱባይ ሌሎቹም ወደ ተለያዩ ሀገሮች እያሸሹ ሲሆን በተለይ የወያኔ በለስልጣናት እና ቤተሰቦቻቸው በሚገርም ሁኔታ ወደ ውጭ ሀገር ገንዘብ እያሸሹ መሆኑንም የደረሰን ጥቆማ ገልፆዋል::

በአሁኑ ሰዓት ህዝቡ የእለት ጉርስ የሚቀምሰው አጥቶ እየተንከላወሰ ባለበት በዚህ ግዜ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ መጠን የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት በሚስቶቻቸውና በዘመዶቻቸው ስም ወደ ውጭ እያስወጡ መሆኑ በእጅጉ አስገራሚ እንደሆነም እየተነገረ ይገኛል::

ለይምሰል ብቻ ዝቅተኛና ተራ ካድሬዎችን በሙስና ሰበብ ክስ እየመሰረቱባቸው ወደ እስር ቤት ቢያስገቡዋቸውም ዋናውና የሀገሪቱን ሀብት እና ንብረት አግበስብሰው በውጭ ሀገር ባንኮች በዘመዶቻቸውና በሚስቶቻቸው ስም ያስቀመጡት የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት መሆኑ እየታወቀ

ህዝቡን እና የዓለም ህብረተሰብን ለማታለል ሲሉ በትናንሾቹ ካድሬዎች ላይ መዝመታቸው የግዜ መግዣ ማድረጋቸውን የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ይገልፃሉ።

ወያኔ ያወጣቸው ሁለት አዋጆች ህዝቡን እያመሱት ባለበት በዚህ ግዜ በፍራቻ እና በድንጋጤ ከባንክ ገንዘብ እያወጡ በቤት ውስጥ ማስቀመጥ በመጀመራቸው የባንክ እንቅስቃሴ እየተዳከመ እንደሚገኝም ለማየት ተችሎዋል።

ወያኔ ሰሞኑን ያወጣው የመሬት ሊዝ ህግ ህዝቡ ላይ ጫና ለማድረግና ቀጥተኛ ተገዥ ለማደረግ ታስቦ የወጣ መሆኑን የጠቀሱት የኢኮኖሚ ባለሙያዎች በተለይ ዜጋው መሸጥ፤ መለወጥ፤ ማስያዝ እንዲሁም የማውረስ ስልጣኑን ሁሉ የተገፈፈበት ነው ሲሉም የተቻሉ።

ከሊዝ ህጉ ጋር በተጉዋዳኝ የአከራይ ተከራይ ተብሎ የወጣው አዋጅ ደግሞ ህዝቡን እያመሰ ከመሆኑም በላይ እርስ በርስ እያጋደሉ እንደሚገኝም ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል።

ወያኔ በውስጥ ችግሩ ተወጥሮ ሊፈነዳ ባለበት ግዜ ጥቂት ባለስልጣናቱ ብቻ በመከሩበት እና በዶለቱበት በዚሁ አዲስ ህግ ህዝቡ እርስ በርሱ እንዲጫረስ እና እንዲከፋፈል በሚል ቀመር የሰሩት ቢሆንም በአብዛኛው ህጉን ተፈጻሚ ላለማድረግ ቃል እየተገባባ መሆኑም ታውቆዋል።

በአንድ ወቅት የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ባለሀብቶችንና ነጋዴዎችን በቤተመንግስት መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ጠርቶ ባነጋገረበት ወቅት እኛን ለመጣል እየገዘገዛችሁን መሆኑን እያወቀን ስለሆነ አብረን ተያይዘን ገደል እንገባለን እንጂ አንላቀቅም በማለት ሲያስፈራራ እንደነበር ያስታወሱት አንድ የመርካቶ ነጋዴ ወያኔዎች ዛሬ እኛን እርስ በርስ ለመከፋፈል ብለው የጀመሩት ስልት በመሆኑ አውቀን ሴራውን ልናከሽፍ ይገባናል ሲሉም ጨምረው ገልፀዋል።